# የብልግና ፓርቲ መግለጫና ውንብድናው!!!

ብልግና ለሁለት ቀናት ያደረገውን ስብሰባ ማጠናቀቁንና የወሰዳቸውን ባለ 10 ነጥብ የውሳኔ ሐሳቦችን የያዘ መግለጫ ከሰዓታት በፊት አውጥቷል!!!

የውሳኔ ሐሳባቸውን  እያንዳንዳቸውን ገልጦ ማየት ያስፈልጋልና ወደዚያው እናልፋለን፦

ፓርቲው በአንደኛው የውሳኔ ሐሳቡ ላይ "...ይህ ስግብግብ ጁንታ በአጭር ጊዜ እንዲፈርስና ሀገራችን ከዚህ ከሃዲ ኃይል ነጻ እንድትወጣ ጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን፣ የአማራና አፋር ክልሎች ልዩ ኃይልና ሚሊሻ እንዲሁም በተለያየ ደረጃ ድጋፍ ላደረጉ መላዉ የሀገራችን ሕዝቦች ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን!" ብሏል!!!

"ጁንታውን ለማፈራረስ!" የምትለዋን ቃል አስምሩባት። አይደለምና ወያኔን ጁንታ የሚሏቸውን ጥቂት ቁጥር  ያላቸውን ወንጀለኞች እንኳ ለመደምሰስ ወይም ለማጥፋት የተወሰደና የሚወሰድም እርምጃ አልነበረም አይኖርምም!" ማለታቸው እንደሆነ ልብ በሉ። ግልጽ ሆኖላቹሃል ግን??? ስለዚህ ከዚህ በኋላ እንኳንና እንደፓርቲ በወያኔ ላይ የሚወሰድ እርምጃ ሊኖር ይቅርና "ጁንታ!" በሚሉት ቡድንም ላይ እንኳ "ከዚህ በላይ የሚወሰድ እርምጃ የለም። ለመበታተን ነበረ የተነሣነው በታትነናቸዋል mission accomplished!" እያሏቹህ ነው ያሉት!!!

በ2ኛው. የውሳኔ ሐሳባቸው ደግሞ "ሕግ ለማስከበር በተደረገው ጥረት የተፈናቀሉ ትግሮችን ወደቀያቸው ለመመለስና ለማቋቋም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲረባረብ እንጠይቃለን!" ይላል!!!

እነኝህ "ተፈናቀሉ!" የሚሏቸው እነማንን እንደሆነ ገብቷቹሃል አይደል??? እነማንን መሰላቹህ እስከአሁን ባለው ጊዜ ከ2292 ንጹሐን የማይካድራ ወገኖቻችንን በአማራነታቸው መርጠው አርደው ወደ ሱዳን የፈረጠጡትን ሳምሪ የሚሏቸውን የአሸባሪ ቡድን አባላትንና ባል የልጆቹን እናት፣ ሚስት ደግሞ የልጆቿን አባት ጎረቤቶቻቸውንም ጭምር ጨፍጭፈው ወደ ትግራይ የፈረጠጡትን ወያኔ ከትግራይ አምጥቶ ወልቃይት ሑመራ... አስፍሯቸው የነበሩ አረመኔዎችን ነው የተፈናቀሉና ወደቀያቸው መልሶ ለሚቋቋም የሚለው። አይገርምም???

ከዚህ በላይ ስድብና ንቀት አለ ወይ ወገን??? የዋሁ ወገኔ "እነኝህን ወያኔ ከትግራይ አምጥቶ አስፍሮ መላ ዘመናቸውን የወልቃይትን አማራ ሲያርዱ የኖሩ አሸባሪ ሰፋሪዎቹን ለማስፈር ብሎ እኛን ወዳፈናቀለን ቀያችን፣ ቤታችንና እርሻችን ልንመለስ ነው!" ብሎ ተሰዶ ባለበት ስፍራ ሁሉ ደስታ ሊገለው ነው እነሱ አራጆችን "ሰፍረውበት ወደነበረው ቦታ መልሰን ልናቋቁም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለድጋፍ ተረባረብ!" ብለው ቁጭ አሉ። ከወያኔ ግድያ

አምልጦ ለሠላሳና አርባ ዓመታት ከቀየው፣ ከጎጆው፣ ከእርሻው ተፈናቅሎ ሱዳን በስደት ተሰቃይቶ እየኖረ ያለው ከሠላሳ ሽህ በላይ የሆነውን ስደተኛ አማራ፣ በሀገር ውስጥም ወደተላያየ ስፍራ ተበታትኖ በድህነት እየማቀቀ ኑሮውን እየገፋ ያለውን ባለ ሀገሩን ባለ ርስቱን አማራ ነው መመለስ የሚገባው ወይስ ወትሮውንም ቦታው ያልሆነውን አፈናቃይ ሰፋሪ??? ፍትሕ የለምና አሁንም ዳኞቹ ወንበዴዎች ናቸውና እንደምታዩት ተፈናቃዩ፣ ተሳዳጁ፣ ተጨፍጫፊው፣ ቤት ንብረቱንና እርሻውን የተቀማው እያለ አፈናቃዩን፣ አሳዳጁን፣ ጨፍጫፊውን፣ የሰውን ቤት ንብረትና እርሻ ቀሚውን መልሰን በማስፈር እናቋቁማለን ነው እየተባልክ ያለኸው ወገን ወገብህን ጠበቅ አድርግ!!!

3ኛው. "በኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥትና ብሔረ መንግሥት ግንባታ ሒደት የተለያዩ የፖለቲካ ኃይል አሰላለፎች የሚታዩበት ነው...!" እያለ ይቀባጥራል። ለመሆኑ በሀገራችን ሀገረ መንግሥት (state building) ለመመሥረት ተለፋ ተደከመ እንጅ መቸና የትስ ነው ብሔረ መንግሥት (nation building) ታስቦና ተሞክሮስ የሚያውቀው???

በሀገራችን "ያለ አማርኛ በስተቀር ሌላ ቋንቋ የሚናገር ሰው ቢኖር፣ ከአማራ ባሕል በስተቀር ሌላ ባሕል የሚያራምድ ሰው ቢኖር ከፍ ብሎ አንገቱን ዝቅ ብሎ ባቱን ይቆረጣል!" የሚል አዋጅ አስነግሮ የተንቀሳቀሰ መንግሥት ኖሮ ያውቃል እንዴ??? ማን ነው ይሄንን ያደረገው ንጉሥ??? መቸና የትስ ነው ይሄንን ያደረገው??? እነሱ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚጀምሩት ከዐፄ ምኒልክ 2ኛ. ነውና "ይሄንን አድርጓል!" የሚሉት ዐፄ ምኒልክን ነው? ፣ ወይስ ልጅ ኢያሱን ነው? ፣ ወይስ ንግሥት ዘውዲቱን ነው? ፣ ወይስ ዐፄ ኃይለሥላሴን ነው??? እስኪ ማን በየትኛው አዋጅና የት ይሄንን እንዳደረገ ከመላ የኢትዮጵያ ታሪክም ቢሆን ጠቅሰውና መረጃ አቅርበው ይንገሩን???

4ኛው. "ለማንነት ጥያቄዎች... የሕዝቡን ነጻ ፍላጎት ከግምት ባስገባ መልኩ ሕጋዊ አሠራርን ተከትሎ ምላሽ እንዲሰጣቸው ኮሚቴው አቅጣጫ አስቀምጧል!" ይላል። ምን ማለቱ እንደሆነ ገብቷቹሀል??? እነሱ "ሕጋዊ አሠራር!" የሚሉት ሰፋሪ አፈናቃይ ግፈኛው ድምፅ እንዲሰጥና የሰው መሬት እንዲወስድ የሚያስችለውን "ሕገመንግሥት" የሚሉትን የውንብድና ሕጋቸውን እንደሆነ ልብ በሉ!!! ምክንያቱም ከቀናት በፊት ባደረጉት ተመሳሳይ ስብሰባና ከስብሰባው በኋላ በሰጡት መግለጫ እንደሰማቹሀት "የወልቃይት ጠገዴ ሑመራ ጠለምትንና ራያ ሕዝብ ጥያቄ የልማትና የፍትሕ እንጅ የማንነት አይደለም!" በማለት በአቶ ብናልፍ አንዷለም በኩል መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳልና ይሄ አገዛዝ ለወልቃይት ጠገዴ ሑመራ ጠለምትንና ራያ ሕዝብ የማንነት ጥያቄ ፍትሐዊ ዳኝነት ይሰጣል ብላቹሀ አትጠብቁ!!!

5ኛው. "በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች በንጹሐን ዜጎች ላይ የሚፈጸሙ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በአፋጣኝ እንዲቆሙ ተገቢው እርምጃ ሁሉ እንዲወሰድ ኮሚቴው ከስምምነት ደርሷል....!" ይላል!!!

አገዛዙ እስከአሁን በማንነታቸው ለተጨፈጨፉት ወገኖቻችን የጸጥታ ኃይሉ ሥራውን በአግባቡ ላለመሥራቱ፣ ሆን ብሎ ለማስጨፍጨፉና ለመጨፍጨፉ ተጠያቂው "ጁንታ!" የሚለው ቡድን እንደሆነ መናገሩ ይታወሳል። ይሁንና ግን ማንነትን መሠረት አድርጎ እየተፈጸመ ያለው ጭፍጨፋ ወይም በአማራ ላይ የሚፈጸመው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ የጸጥታ ኃይሉ "ከጁንታው ጸድቷል!" ካሉን በኋላም ይሄው እስከአሁኗ ሰዓት ድረስ በተቀናጀና በተቀናበረ መልኩ ጭፍጨፋው ተፏፋሞ እየተፈጸመ መገኘቱ ለዚህ ዓለምአቀፋዊ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠያቂውና ችግሩ ያለው በአጠቃላዩ ሥርዓቱ መሆኑን ያረጋግጣልና አጠቃላይ የአገዛዙ ባለሥልጣናት ተጠያቂዎች ናቸው!!!

6ኛው. " የአገራችንን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ለመፍታት በሚደረጉ ጥረቶች በየትኛውም ቦታ የሚገኙ የብልጽግና አመራሮችና አባላት ከሚለያዩ ጥቃቅን ጉዳዮች ወጥተው ከፍ ያለ ሀገራዊ ዕይታ በመያዝ ኢትዮጵያንና የሁሉንም ዜጎቿን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን በሚያደርግ መልኩ እንዲደጋገፉ፣ እንዲረዳዱ፣ በአብሮነትና በትብብር መንፈስ መሥራት እንደሚገባቸው አቅጣጫ ተቀምጧል!" ይላል!!!

ስለዚህ እንደ አቶ ታዬ ደንድአና አቶ አዲሱ አረጋ ያሉት ከሥልጣንና ኃላፊነታቸው ውጭ በማያገባቸው እየገቡ የሚዘላብዱት መዘላበዳቸውን ያቆማሉ ማለት ነው??? እንግዲህ ይሄንን በቀጣይ ቀናት የምናየው ይሆናል። እኔ ግን አይመስለኝም። ሀቁ ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ይባል በነበረ ጊዜና አሁንም ብልግና በሚባልበት ጊዜ የጎሳ ፌዴሬሽንን ላለመተው የቆረጠ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ሲያደርግ እንደምናየው በምንም ተአምር ቢሆን አንድ ሀገርንና ሕዝብን ሕልሙ ጉዳዩ አድርጎ ሊሠራ የማይችል መሆኑ ነው። በመሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእነዚህ ጠባብ የጎሳ ልክፍተኞች ተጨማሪ ዕድል ሊሰጥ አይገባም። ለነገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቸ ዕድል ሰጥቷቸው ያውቅና???

7ኛው. " በ2013 ዓ.ም. የሚካሔደው ምርጫ ሀገራችን ወደ እውነተኛ የዲሞክራሲ ሥርዓት ለምታደርገው ሽግግር ያለው ትርጉም እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል። የሚካሔደው ምርጫ ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ነጻና በሒደቱም ሆነ በውጤቱ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሆኖ እንዲጠናቀቅ የብልጽግና አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች በከፍተኛ ቁርጠኝነት እንዲሠሩ አቅጣጫ ተቀምጧል!" ይላል። ነገር ግን እስከአሁን ባለው ጊዜ የምርጫ ቦርድ ተብየውም ሆነ የብልግና ፓርቲ እያሳዩን ያሉት ነገር ሁሉ ይሄንን የሚያረጋግጥ አይደለም። ስለሆነም "ለማያውቅሽ ታጠኝ!" እንላለን!!

8ኛው. "ብልጽግና ፓርቲ በመጪው ምርጫ ጠንካራ ተወዳዳሪ ሆኖ በውጤታማነት እንዲያጠናቅቅ በፓርቲው ማኒፌስቶ ላይ በጥልቀት ተወያይቶ አጽድቆታል። መላው የፓርቲው አመራሮችና አባላት የጸደቀውን ማኒፌስቶ መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ አቅጣጫ ተቀምጧል!" ይላል!!!

ነገር ግን ዝግጅቱ ለዚህ ሳይሆን አገዛዙ ከዚህ ቀደም ሲያደርገው እንደኖረው ሁሉ አሁንም ከምርጫ ቦርድ ተብየው ጋር በመመሳጠር ምርጫን አጭበርብሮ ለማሸነፍ ሁለት መቶ ሐምሳ ሽውን የምርጫ አስፈጻሚ አባላት በሙሉ በራሱ አባላት ሞልቶ ተዘጋጅቷል። መሆን የነበረበት ግን ሕዝቡ በቂ የትምህርት ዝግጅት ካላቸውና የየትኛውም ፓርቲ አባላት ካልሆኑ ዜጎች መርጦ እንዲያቀርብ ነበር መደረግ የነበረበት። በመሆኑም በዚህ ነጥብ ላይ የተገለጠው አቋም ነጭ ውሸት ነው!!!

9ኛው. "በአገራችን በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ እውነተኛ የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመሸጋገር የተወሰዱ የአገራዊ ለውጥ እርምጃዎችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ነጻና በሒደቱም ሆነ በውጤቱ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሆኖ እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪ እናቀርባለን!" ይላል!!!

ነገር ግን እራሱ ብልግና ፓርቲም ምርጫ ቦርዱ የራሱ ስለሆነ መስፈርት አሟልቶ የተመዘገበና ሕጋዊነት ያለው መስሎ ይንቀሳቀሳል እንጅ መስፈርቱን አሟልቶ ማለትም ጠቅላላ ጉባኤ አድርጎ ሊቀመንበር ምክትል ሊቀመንበር... መርጦ፣ የፓርቲ ደንብ ቀርጾ... ለምርጫ ቦርድ አስረክቦ የተመዘገበና ፈቃድ የተሰጠው ሕጋዊ ፓርቲ ባለመሆኑ ሌሎችን ፓርቲዎች ይሄንን የማለት የሞራል ብቃት የለውም!!!

10ኛው. "መላው የአገሪቱ ሕዝቦች ባለፉት ሁለት ተኩል ዓመታት በኢትዮጵያ የታዩ ለውጦችና የተገኙ ድሎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ መጪው ሀገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ነጻና ተቀባይነት ያለው ሆኖ እንዲጠናቀቅና የዜጎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ብልጽግና የተረጋገጠባት ጠንካራ ሀገር ለመገንባት በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ሁሉ እንዲያደርጉ ጥሪ እናቀርባለን!" ይላል!!!

እኔ ደግሞ አገዛዙ ይሄንን ጥሪ መልሶ ለራሱ እንዲያሰማው እጠይቃለሁ። ከሱና ቡችሎቹ ውጭ ለነጻ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ ሥጋት የሆነ ሌላ አካል የለምና። ነውጥ እንጅ ለውጥ የሚባል

ነገር በሌለበት ሁኔታ እንዲህ ሲሉ አለማፈራቸው ነው የሚገርመኝ። በጭፍጨፋው፣ በዘረኝነቱ፣ በዝርፊያው፣ በውንብድናው በየትኛው ነው ለመሆኑ ይሄኛው የአገዛዝ ዘመናቸው ከፊተኛው የአገዛዝ ዘመናቸው የተሻለ ሆኖ ትንሽ እንኳ ሳያፍሩ "ለውጥ!" የሚሉን ለመሆኑ???

ወደ መደምደሚያየ ስሻገር እንዲያው ነገሩን አልኩና እያንዳንዱን ነጥብ ተቸሁ እንጅ ሲጀመር እነሱ ይሄንን ያሉትን ነገር ሁሉ ለሕዝብም ሆነ ለመንግሥት አካላት እንዲሁም ለፓርቲዎች… የማለት መብት ያለው መንግሥት ተብየው እንጅ ፓርቲ አይደለም። በዚህ መልኩ ከሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት መፍጠር የሚችለው መንግሥት እንጅ ፓርቲ አይደለም። ብልግና ፓርቲ የመንግሥት ተብየውን ሰዓት ሰርቆ፣ የመንግሥትን ንብረትና ገንዘብ ተጠቅሞ የፓርቲ ስብሰባ እንዲያደርግና እንዲህ ዓይነት ውሳኔ እንዲያሳልፍ የትኛው ሕግ ነው የፈቀደለት ለመሆኑ??? ትክክለኛ የምርጫ ቦርድና ሕግ አስፈጻሚ በዚህች ሀገር ቢኖር ኖሮ ተለቃቅመው መጎኒ መወርወር ነበረባቸው። በጣም የሚገርመኝ ነገር አገዛዙ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ ወንጀል ሲፈጽም ከፓርቲ ተብየዎች አንድ እንኳ ክስ የሚያሰማ ፓርቲ አለመኖሩ ነው!!! አያሳዝንም???

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው